የሚገኘው የኢትዮጵያ አብዮት ዝር ዝር የተከሳሸ አብዮት ሆኖ ይቀራል ማለት ነው።

በኢትዮጵያ የተራማጆች ድርጅቶች መካከል በልዩ ልዩ ነጥቦች ላይ ልዩነቶች እንዳሉ የታወቀ ነገር ነው።በነዚህ ነጥቦች ላይ ሰፋ ያለና ግልጽ ውይይት መካሄዱ ይኖርበታል። መኢሶን በበኩሉ ለዚህ አይነት ውይይት መቸውንም ቢሆን ዝግጁ ነው።አንዳንድ ጓዶችና ቡድኖች ይህ ውይይት ተራማጆችን ይከፋፍልና በተለይ አሁን የኢትዮጵያ አብዮት በአደጋ ላይ በለበት ሁኔታ የሰፊውን ህዝብ ትግል ያዳክማል የሚል እምነት አላቸው።መከፋፈሉና መዳከም የሚያመጣው ይልቁንስ ... ጥብቅ ውይይት በሌለበት ሁኔታ በፕሪንሲፕል ላይ ያለቅጥ ህብረትን ወይንም አንድነትን ለመፍጠር መቻኮሉ ነው።

በተረፈ ግን አሁንም መኢሶን መቶ ጊዜ ይበልጥ በወዛደሩና በድሃ ገበሬው ውስጥ መተከል አለበት እንላለን።መቸስ ነገ የኢትዮጵያ ወዛደር ፓርቲ ይፈጠራል ስለተባለ እያንዳንዱ ተራማጅ ቡድን ለራሱ ድርጅት መስራቱን ትቶ ወደ ሌላ ቡድን ወይንም እንዲያው በደፈናው ''ለወዛደሩ ፓርቲ'' ብቻ ቀበቀባን ሊያካሂድ አይችልም።በማርክሲዝም—ሌኒኒዝም በመመራት ከታገለ፣ የረጅሙን ጊዜ አላማዎች ለእለታዊ ጥቅሞች ካልሰዋና በጠባብ ቡድን መንፈስ ካልተመረዘ፣ የያንዳንዱ ተራማጅ ድርጅት መስፋፋት ለአብዮቱ መቀጠል ዋስትና እንጂ በምንም መንገድ እንቅፋት አይሆንም።ይህ ስለተባለ ግን ባሁኑ ሰአት መቀራረብ፣ ህብረትን መፍጠርና አንድ ጠንካራ የወዛደር ፓርቲን ለመመስረት መታገል የለብንም ማለታችን እንዳይደለ ግልጽ ነው።ሁለቱም ትግሎች፣-ማለትም የያንዳንዱ ቡድን መጠናከርና የቡድኖቹም መቀራረብ፣ ባንድ ላይ የሚካሄዱ ነገሮች ናቸው።

ኢህአፓና አድሃሪያች ሁሉ ይውደሙ!
ለሃቀኛ የተራማጆች ህብረት እንታገል!
እውነተኛ የወዛደሩን ፓርቲ ለመመስረት እንታገል!!